# ውይይቱ በየእናቴ መቀነት አደናቀፈኝ

# እንዳይጠለፍ . . .

ዮናስ 02-10-17

ኢህአዴግ ሃገሪቱን ከተቆጣጠረ 1983 ዓ/ም ጀምሮ በሃገራችን 5 ሃገር አቀፍ ምርጫዎች ተካሂደዋል። በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዙር ምርጫዎች የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ ሃይሎች በየደረጃው በሚገኙ ምክር ቤቶች "የተሻለ" የሚባል ወንበርና የመንግስትን ስልጣን ይዘው የነበረ መሆኑ ይታወቃል። ምንም እንኳን በ3ኛው ዙር በነበረው ምርጫ ከሁሉ የላቀ ወንበር ያገኙ ቢሆንም ከመጠቅለል አባዜ በመነሳትና እርስ በራሳቸው በፈጠሩት ሽኩቻ እድላቸውን ሳይጠቀሙ የቀሩ መሆኑም በተመሳሳይ ይታወቃል። በአብዛኛው ከእነርሱ በመነጩ ምክንያቶች ከዚያ በኋላ በነበሩት ምርጫዎች ይዘውት የነበረውን ማጣት ብቻ ሳይሆን ከምክር ቤት መቀመጫዎች ርቀዋል። ይህ ማለት ግን የሚወክሉት ድምጽ የለም ማለት አይደለም፤ አለ።

በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ሂደት ውስጥ፤ በተቃዋሚዎች ችግርም ይሁን በገዢው ፓርቲ ጥንካሬ፣ ምክር ቤቶች በአንድ ፓርቲ ስር እስከቆዩ ድረስ ሂደቱ የሚገታ መሆኑ አያጠያይቅም። ይህን እና መሰል ምክንያቶችን ታሳቢ በማድረግ ከአብላጫ ድምጽ የምርጫ ስርአት በተሻለ የብዙዎችን ድምጽ መወከል የሚችሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን አሳታፊ ሊያደርግ የሚችል እድል የሚፈጥር ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑን በማመን ገዢው ፓርቲ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ውይይት እና ድርድር ለማድረግ መድረክ አዘጋጅቷል።

መንግስትም እንደ መንግስት ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጠው መግለጫ ባለፉት ሁለት ምርጫዎች (በ2002 እና በ2007 ዓ.ም የተካሄዱትን ለማለት ነው) የገዥው ፓርቲ የበላይነት ሙሉ በሙሉ የተከሰተበት በመሆኑ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ተሳትፎ ተገድቦ እንደነበር በማስታወስና አጽንኦት በመስጠት ነው። በመሆኑም መንግስት ዴሞክራሲያዊ ስርዓታችን ተረጋግቶ እንዲቀጥል ካለው ፈላጎት በመነሳት እና በሃገራችን ያለውን የፍላጎት ብዝሃነት በመገንዘብ ዴሞክራሲያዊ መድረኮችን በማስፋት በሰላማዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ውይይት፣ ድርድርና ክርክር ማካሄድ ብሎም ህጎችን እስከማሻሻል ድረስ መሄድ እንዳለበት ቁረጠኝነቱን አሳይቷል ብሎ መውሰድ የሚቻልና ከተቃዋሚውም በኩል ተመሳሳይ ቁርጠኝነት የሚጠበቅ መሆኑን ያመላክታል።

በአገራችን ወሳኙ የስልጣን አካል የሆኑት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች የተለያዩ ድምጾች የሚሰሙባቸው እና የሚፎካከሩባቸው መድረኮች እንዲሆኑ ለማድረግ የመንግስትን ብቻ ሳይሆን የተቃዋሚውንም ዝግጁነትና ዴሞክራሲያዊነት በእጅጉ ይጠይቃል።

በነገራችን ላይ ከላይ በተመለከተው ምክንያት ድርድሩ ለማካሄድ የታሰበው የፌዴራል መንግስቱ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ መስከረም ላይ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤትን በንግግር ሲከፍቱ የምርጫ ህጉ ይሻሻላል ብለው በተናገሩት እና ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ በአገር ውስጥ በሰላማዊ መንገድ ከሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች ጋር እነጋገራለሁ ባሉት መሰረት ነው።

በአንድ አገር ለሚፈጠር ሰላማዊ የስልጣን ሽግግርና የዴሞክራሲ መሰፋፋት ትልቁ መንገድ በፖለቲካ ተዋንያኖች መካከል የሚካሄድ ድርድርና ውይይት ነው። ሀሳቦች ወደ ጠረጴዛ ቀርበው ውይይት ካልተካሄደባቸው ልዩነቶች እየሰፉ ሂደው መጨረሻው ማጣፊያው እንደሚያጥር በዙሪያችን ያሉ እውነታዎች ምስከሮች ናቸው። የኢትዮጵያን መንግስት አቋም የሚገልጸው ሳምንታዊው የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት እንዳረጋገጠውም ሆነ የፖለቲካ ፓርቲዎች ደጋግመው እንደሚገልጹት፣ በአገራችን የተፈጠረው አለመረጋጋት ምክንያቱ በ2007 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ በሁሉም ደረጃዎች የሚገኙ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች በገዥው ፓርቲ አባላት ብቻ መሞላታቸው ነው፤ በመሆኑም ውይይት አስፈለገ።

እዚህ ጋር  መዘንጋት የሌለበት እና የዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነውም፡- በሃገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ገዥውን ፓርቲ *የፖለቲካ ምህዳሩን አጥብቦ የዴሞክራሲ ስርዓቱን አቀጭጭጯታል* በማለት ሲከሱት የነበረ መሆኑና ይህን እድል የመጠቀምና ያለመጠቀም ጉዳያቸው በህዝብ ዘንድ የሚመዘነውም ይህንኑ ክሳቸውን እና ከላይ የተመለከተውን የመንግስት መነሻ ታሳቢ በማድረግ መሆኑን ነው።

ከ2007 ዓ.ም ምርጫ መጠናቀቅ በኋላ ከላይ በተመለከተው አግባብ በምርጫ ስርአት ያልተሳካላቸው ሃይሎች ከውስጥና ከውጭ ሆነው አንዳንዴም የውጭ ቅጥረኛ ሃይሎችን አክለው በአገሪቱ በተለይም በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች አመጾችንና ግጭቶችን አስነስተው የነበረ መሆኑንም ባለመዘንጋት፤ በእርግጥም ችግራቸው የምህዳር ጉዳይ ከሆነ ይህን እድል በአግባቡ ሊጠቀሙ ግድና ግድ መሆኑ የመጀመሪያው አመክንዮ ነው።

ለአመጾቹና ለግጭቶቹ መንስዔ መንግስት የሰጠው ምላሽ “የመልካም አስተዳደርና ለወጣቶች በቂ የስራ እድል አለመፈጠር” የሚል ሲሆን፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በበኩላቸው “መንግስት የህዝብን ድምጽ በማፈኑ ነው” ሲሉ መከራከራቸው የሚታወቅና ስለአፈናውም በምክንያትነት ከሚጠቅሱት መካከል ይኸው የምርጫ ስርአት መሆኑን ህዝቡ ያውቃልና ያለፈውን በመቧጠጥ በድርድሩ ላይ ለ“የእናቴ መቀነት አደናቀፈኝ” ጆሮ የሚኖረው ዜጋ ይኖራል ተብሎ አይጠበቅም።

በዚሁ መሰረት የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ለሚያደርጉት ውይይት መደላድል እንዲሆን ቅድመ ዝግጅቱ ባሳለፍነው ሳምንት በፌዴሬሽን ምክር ቤት አዳራሽ ባለድርሻዎቹ ባሉበት ተካሂዷል። ያም ሆኖ ግን ከላይ በተመለከተው አግባብ *ምህዳሩ ጠቧል፤ ምክር ቤቶች በአንድ ፓርቲ አባላት ተይዘዋል* ሲሉ የከረሙ ሃይሎች ገና በቅድመ ዝግጅቱ ማግስት የናቴ መቀነት ጠለፈኝን እየሰበኩና ሂደቱን ለማደናቀፍ እየሰሩ ስለመሆኑ አመላካች የሆኑ ፍንጮችን እያሳዩ ይመስላል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክ ሊቀመንበረ ፐሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ በጉዳዩ ዙሪያ አስተያየታቸውን ለሰንደቅ ጋዜጣ ሲሰጡ “በቅድመ ውይይት ወይም ድርድር ዝግጅት ስብሰባችን ላይ በእኛ በኩል ለእውነተኛ ድርድር የሚመቸንን ቅድመ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችለንን ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀምጠናል” ማለታቸው የተለመደውን የቅድመ ሁኔታ የዜሮ ድምር ጫወታ በመጫወት ድርድሩን በዜሮ አባዝተው ሊወጡ ስለማሰባቸው ፍንጭ የሚሰጥ የመጀመሪያው አስረጅ ነው።

የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ የሽዋስ አሰፋ ደግሞ "ከመስከረም ጀምሮ ገዥውን ፓርቲና ተቃዋሚዎችን ለማወያየት የሚጥሩ ሰዎች እንደነበሩ እናውቃለን። ጥሪውን እንጠብቅ የነበረው ከእነዚያ ሰዎች ቢሆንም ኢህአዴግ ጣልቃ ገብቶ የድርድር ፕሮግራሙን ጠርቷል። ኢህአዴግ *በራሴ ተነሳሽነት ነው የጠራሁት* ብሎ ካመነ እንደለመደው ለፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ ፈጆታ ሳያውለው ከፍተኛ ዋጋ ባላቸው አገራዊ ጉዳዮች ላይ በግልጽነት፣ በጋራ ልንወያይ ይገባል" ሲሉ ከመሰረታዊው አጀንዳ ያፈነገጠና እገሌ ስለጠራው እገሌ ህዝብ የማያገባውን ጉዳይ በመጥቀስ ለ*የእናቴ መቀነት ጠለፈኝ*ማቆብቆባቸውም ሁለተኛው አስረጅ ነው።

እዚህ ጋር ግን የኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ) በሊቀመንበሩ ዶክተር ጫኔ ከበደ በኩል "ኢህአዴግ ይህን ድርድር ማዘጋጀቱ እንደ ፓርቲያችን የገመገምነው በመልካም ጎኑ ነው" ጠሪና ተጠሪውን ሳይሆን አላማው ላይ ትኩረት ያደረገ አስተያየት የመስጠታቸውን ቁርጠኝነት ማድነቅ ተገቢ ይሆናል።

የዴሞክራሲያዊ ስርአትን ወሳኝነትና ስለሃገራችን ብልጽግና ያለውን የማይተካ ሚና ታሳቢ በማድረግ ለተጠራው የድርድር መድረክ ከላይ የተመለከቱት ተቃዋሚ ሃይሎች ካቀረቧቸው ቅድመ ሁኔታዎች ጥቂቶቹን በመጥቀስ ምን ያህል *በእናቴ መቀነት ጠለፈኝ*የዜሮ ድምር ፖለቲካ ለመጫወት እንደተዘጋጁ ማረጋገጥ ይቻላል።

*የታሰሩ አባሎቻችን እና መሪዎቻችን ይፈቱ፤ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ይነሳ* የሚሉት እና ከምርጫና ከፖለቲካ ጋር የማይገናኙ የህግ ጉዳዮች በቅድመ ሁኔታነት ከቀረቡት መካከል የሚጠቀሱና *ለእናቴ መቀነተ ጠለፈኝ* ፖለቲካ አስረጅ የሚሆኑ ናቸው። በምናደርገው ውይይት ላይ በገለልተኛ የዓለም አቀፍም ሆነ አገር አቀፍ ታዛቢዎች መገኘት አለባቸው የሚለውና የውጭ ሃይሎችን ናፋቂነት የተመለከተው ቅድመ ሁኔታም ሌላኛው እና ስለናቴ መቀነት ጠለፈኝ ፖለቲካቸው ሊጠቀስ የሚገባው ነው፡፡ ከእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች በተጨማሪም "የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል፤ ይመለከተኛል የሚሉ በውጭ አገር የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎችም በውይይቱ (በድርድሩ) በተሳታፊነት ወይም በታዛቢነት እንዲገኙ ጥሪ ሊቀርብላቸው ይገባል" የሚለው እና *አሸባሪዎችን ሳይቀር ይጋበዙ* የሚለው ቅድመ ሁኔታ የዚህች ሃገር ችግር የሚፈታው ሃገር ውስጥ ተቀምጠው በሚታገሉ ሃይሎች እንጂ ባህር ማዶ በሚገኙ ፓርቲዎች አይደለም ሲሉ ለወትሮው ከምናውቃቸው ፓርቲዎች መቅረቡ በናቴ መቀነት ጠለፈኝ ፖለቲካ ድርድሩን ለማኮላሸት እየሰሩ መሆኑን ከወዲሁ የዚህ ድርድር ተጠቃሚ እና በስሙ የሚነገድበት ህብረተሰብ ጠንቅቆ ሊገነዘብ ይገባል።

22 አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገራቸው ጉዳይ ላይ ለመወያየት (መደራደር) በገዥው ፓርቲ (ኢህአዴግ) ጥሪ አማካኝነት ጥር 10 ቀን 2009 ዓ.ም በፌዴሬሽን ምክር ቤት ተሰባስበው ስለ ድርድሩ አካሄድ ውይይት ከጀመሩ በኋላ በውይይቱ በአጀንዳነት ሊያዙ ይገባል የሚሏቸውን ነጥቦች ጠቅሰው እስከ ጥር 25 ቀን ድረስ እንዲያስገቡ (በፓርላማ የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትር በኩል) ተነግሯቸው ተለያይተዋል።

እኛም ጉዳዩን በሀላፊነት ስሜት አስበውና መክረውበት ለአገር የሚበጀውን ሁሉ ይዘው ይመጣሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።